# ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

## ይድረስ፦ ለቅዱሱ ኪዳን፡

## "የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም ልጆች!"

## እየራሳችሁን፡ ለዚህ ታላቅ ኪዳናዊ ጸጋ እንደምታበቁ ለታመነባችሁ፡ ለተወደዳችሁ አንባቢዎቻችንም!

### አንድ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ርእሰ ብሔር፡ በክቡር አቶ ባሮክ ሁሴን ኦባማ አማካይነት፡ በ"ኢትዮጵያ" ምድር፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገውን፡ የይፋ ጒብኝት በሚመለከት፡ የተላለፈላችሁ መልእክት።

\+ + +

በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ስም፡
ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በያላችሁበት እናቀርብላችኋለን።

### የ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"
### ማንነትና ምንነት፡ ባጭሩ።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የማይታዩትንና የሚታዩትን፥ ረቂቃኑንና ግዙፋኑን፥ ሰማያውያኑንና ምድራውያኑን ፍጥረታተ ዓለማት ያስገኘች፥ እነርሱንም፡ በፈጣሪነትና በባለቤት፥ በሃይማኖትነትና በምግባርነት፥ በአባትነትና በእናትነት፥ በሊቀ ካህናትነትና በቤተ መቅደስነት፥ በንጉሥነትና በንግሥትነት፡ በምልዓትና በሥርዓት የምትመራና የምታስተዳድር፥ የምትመግብና የምትጠብቅ መኾኗን አውቃችኋል፤ አምናችኋልም።

አዎን! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ ማንነቷና ምንነቷ፡ በተለይ፡ በምድራዊውና በሥጋዊው ፍጥረተ ዓለም ዘንድ፡ እነሆ! እስከዛሬ፡ ለ፯፻፭፻፯ (ለሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባት) ዓመታት፡ ጸንታና ገሃድ ኾና የኖረች፥ አኹንም፡ እየኖረች ያለች፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም የምትኖር መኾኗን፡ መቸም፡ ጥንት ከመሠረቱ፡ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ "የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች!" የኾኑት፥ ዛሬም፡ የኾናችሁት፥ ለወደፊትም፡ እየራሳችሁን፡ እንዲህ ለማኾን የተዘጋጃችሁት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ኹሉ፡ ማወቅና ማመን ብቻ ሳይኾን፡ ሕይወት አድርጋችሁትም፡ ይኸው እየኖራችሁት ትገኛላችሁ።

የዚህ መለኮታዊ ጸጋና በረከት፡ ተካፋዮች ለመኾን የቻላችሁት፡ እናንተ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ኹሉ፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሢሕ፡ እንዲህ ሲል፡ ለተናገረው ቃል፡ እየራሳችሁን በማብቃታችሁ መኾኑ፡ የኪዳናዊው ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ ፍሬ በኾነው፡ በዚሁ ሕይወታችሁ፡ ተረጋግጦ ታውቋል።

"አማን እብለክሙ! ከመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን፡ ፈተዉ ይርአዩ፡ ዘትሬእዩ፤ ወኢርእዩ። ወፈተዉ ይስምዑ፡ አንትሙ ዘትሰምዑ፤ ወኢሰምዑ። ወለክሙሰ፡ ብፁዓት አዕይንቲክሙ፡ እስመ ይሬእያ። ወዕዘኒክሙ፡ እስመ ይሰምዓ።"

ማለትም፡ "እውነት እላችኋለሁ! ብዙዎች ነቢያትና እውነተኞች፡ እናንተ፡ ዛሬ የምታዩትን፡ ሊያዩ፡ እጅግ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን፡ አላዩም። እናንተ፡ ዛሬ የምትሰሙትንም፡ ሊሰሙ፡ እጅግ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን፡ አልሰሙም። የእናንተ ግን፡ ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ፥ ጆሮዎቻችሁም ስለሚሰሙ፡ ብፁዓት ናቸው።"

ዳሩ ግን፡ እርሱን በመምሰል ይኖር ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ የፈጠረው፡ አብዛኛው የሰብአዊው ፍጡር ወገን፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ፡ ራሱን፡ ክፉና ሓሳዊ፥ ከሓዲና ዓመፀኛ፥ ጣዖት አምላኪና አመንዝሪ በማድረግ፡ ወደሰይጣናዊነት ስለለወጠ፡ በዚህ፡ በራሱ ኃጢአት ምክንያት፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለዚህን ያህል ረዥም ዘመናት፡ ማለትም፡ ለ፯ሺ፭፻፯ (ለሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባት) ዓመታት፡ ተሠውራው ኖረች።

መራራ ውጤቱ፡ በኖኅና በሎጥ ዘመናት፡ የታዩት፡ ጥፋትና ድምሳሴ የኾኑት፡ ይህን የመሰለው፡ አሳዛኝ ዕድል፡ በዚህ የሰው ወገን ላይ ሊደርስበት የቻለው፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሢሕ፡ እንዲህ ሲል የተናገረው ቃል፡ ሊፈጸም የሚገባ በመኾኑ ነው፡-

"ወበእንተ ዝንቱ፡ በአምሳል እትናገሮሙ፤ እስመ እንዘ ይሬእዩ፡ ኢይሬእዩ። ወእንዘ ይሰምዑ፡ ኢይሰምዑ፤ ወኢይሌብዉ። ከመ ይትፈጸም ላዕሌሆሙ፡ ትንቢተ ኢሳይያስ፤ ዘይቤ፡-

"‹ሰሚዐ፡ ትሰምዑ፤ ወኢትሌብዉ፤ ወነጽሮ፡ ትኔጽሩ፤ ወኢትሬእዩ። እስመ ገዝፈ ልቡ፡ ለዝ ሕዝብ። ወዕዘኒሆሙ፡ ደንቀወ፡ እምሰሚዕ። ወዖሩ አዕይንቲሆሙ፡ ከመ ኢይርአዩ፡ በአዕይንቲሆሙ። ወበዕዘኒሆሙ፡ ኢይስምዑ። ወበልቦሙ፡ ኢይሌብዉ፤ ወኢይትመየጡ ኀቤየ፡ ከመ ኢይሣሃሎሙ።›"

ማለትም፡ "እያዩ፡ ስለማያዩ፥ እየሰሙም፡ ስለማይሰሙ፣ ስለማያስተውሉም፡ ስለዚህ፡ በምሳሌ እነግራቸዋለሁ። ይህም፡-

"‹መስማትን፡ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን፡ አታስተውሉም። መመልከትን፡ ትመለከታላችሁ፤ ነገር ግን፡ አታዩም። የዚህ ሕዝብ፡ ልቡ ደንድኗልና። ጆሮአቸውም፡ ከመስማት ደንቍረዋልና። በዓይኖቻቸው እንዳያዩም፡ ዓይኖቻቸውን አሳውረዋል። ጆሮዎቻቸውም፡ አይሰሙም። በልባቸውም፡ አያስተውሉም። ይቅር እላቸው ዘንድ፡ ወደእኔ፡ በንስሓ አይመለሱም።› የሚለው፡ የኢሳይያስ ትንቢት፡ በእነርሱ ላይ ሊፈጸም፡ ስለተገባ ነው።›" (ማቴ. ፲፫፥ ፲፫-፲፯።)

ዳሩ ግን፡ ይህንና ሌላውን፡ መለኮታዊ የሕይወት ቃል የተናገረላትን፥ በቤዛነቱም፡ ተፃራሪውን የክፋት ኃይል ኹሉ፡ ከሓሰቱና ከሞቱ ጋር፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ በማስወገድ፡ በምድር ላይ፡ በቅድስት እናቱና በራሱ ሰውነት፡ እንደገና ተከሥታ እንድትጸና ያደረጋትን፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ እነዚሁ ክፉዎች ወገኖች፡ እንኳንስ፡ አምነውባት ሊኖሩባት ይቅርና፡ አኹንም እንደገና፡ የማይፈኋትና የማይቀበሏት መኾናቸውን፡ በይፋ አስታወቁ።

"ፈልገናታል! ተቀብለናታል!" የሚሉት፡ አስመሳዮቹና ግብዞቹ ወገኖችም፡ በእርሷ ስም፡ በሓሰትና በሙስና እየተጠቀሙ፡ የሥልጣን ብልግናቸውን ከመቀጠል በቀር፡ በእውነተኛ ማንነቷና ምንነቷ ሊያገለግሏት ባለመፍቀዳቸው፡ እነሆ፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለዚህ፡ ለዛሬው፡ ለመላው የሰው ዘር ትውልድ፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ሊያያት እንዳይቻለው ኾኖ፡ የተሠወረችበት ኾነች።

ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ትውልድ፡ በአስተሳሰቡና በአድራጎቱ፡ ራሱን፡ ያንኑ፥ እንዲያውም፡ በባሰ ኹኔታ የሚታየውን፡ የኖኅንና የሎጥን ጊዜያት በመሰለው፡ በመጨረሻው የጥፋትና የድምሳሴ ዘመን እንዲገኝ አደረገ፤ ደግሞም፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው፡ በራሱ ላይ ባመጣው፡ ኢአማኒቱና ክፋቱ ምክንያት፡ የእግዚአብሔር ልጅነቱን አጥቶ፡ ራሱን፡ ለዲያብሎስ ባርነት ዳረገ።

ስለዚህ፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ ከዚያ ወዲያ፡ በገሃድና በግዘፍ ሊያያት ባለመቻሉ፡ እስካኹን፡ እንዲህ፡ ተሠውራበት ከቆየች በኋላ፡ አኹን፡ ጊዜው ሲደርስ፡ በቸርነቷ፡ ለዚሁ፡ ለመላው ዓለም ሰብኣዊ ፍጡሩዋ፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እነሆ፡ በቅርቡ፡ በዐዋጅና በይፋ፡ ራሷን መግለጧ ይታወሳል።

ራሷን፡ እንዲህ፡ በዐዋጅና በይፋ የገለጠችው፡ ይህች፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሌላ ሳትኾን፡ ያችው፡ በሰማይና በምድር ያሉትን፡ ፍጥረታተ ዓለማቷን፡ በራሷ፡ በእናቲቱ ንግሥት፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና በራሱ፡ በተወዳጁ ካህኑ ንጉሥ ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ሕይወታቸው በኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ ምንጊዜም እየመራችና እያስተዳደረች፥ እየመገበችና እየጠበቀች በኖረችበት፥ ዛሬም፡ ባለችበት ፈጣሪነቷና ባለቤትነቷ፥ አባትነቷና እናትነቷ፥ ሃይማኖትነቷና አገርነቷ፡ እየቀጠለች እንዳለች፡ በዚያው የዐዋጅ ቃሏ አስታውቃለች።

ይህ ኹሉ እግዚአብሔራዊ የኾነው ትንግርት፡ ተካኺዶና ተከናውኖ የተፈጸመው፡ በዚህ ልዩ ዘመን፡ በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ የመኖርን ዕድል በተቀዳጃችሁት፥ ለዚህ ታላቅ ተልእኮም ተጠርታችሁ፡ ጥሪውን፡ በፍጹም ፈቃደኝነት በመቀበል፡ እየራሳችሁን፡ ለክህነታዊው አገልግሎት ባበቃችሁት፡ በእናንተ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆቿ አማካይነት መኾኑ፡ እዚህ ላይ ሊዘከር የሚገባው ነው።

## በኢትዮጵያ፡<br>የ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ርእሰ ብሔር፡<br>የክቡር አቶ ባሮክ ሁሴን ኦባማ፡ የይፋ ጉብኝት።

የዚች፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ጥንታዊትና ሕያውት፥ ዘለዓለማዊትም ቅርስ በኾነችው፥ በ"ኢትዮጵያ" ምድር፡ የይፋ ጉብኝት ለማድረግ፡ የመጀመሪያው፡ የ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ርእሰ ብሔር በመኾን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ የገቡት፥ ጉብኝታቸውንም፡ በመልካም ፈጽመው የተመለሱት፡ የዚያች አገር መሪ፡ ክቡር አቶ ባሮክ ሁሴን ኦባማ ናቸው።

እኚህ ታዋቂ ሰው፡ ስለራሳቸው ትክክለኛ ማንነትና ምንነት፡ እኛ ያወቅነውን ያህል፡ እርሳቸው ራሳቸውም፡ በእውነት ካወቁትና በእምነት ከተቀበሉት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ "የኢትዮጵያ ልጅ" መኾናቸውን የሚያመለክቱ፡ እውነታዎች እንዳሉ፡ ልናሳውቅ እንወድዳለን፤ ከእነዚህ መካከል፡ ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል፡ የሚከተሉትን እናቀርባለን፡-

፩ዱ "ስምን መልአክ ያወጣዋል!" ነውና፡ በልጅነት ስማቸው፡ በግእዙ፡ "ቡሩክ" ወይም "ባሮክ" ተብለው፡ ከኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ጋር፡ የኢትዮጵያዊው ታላቅ ነቢይ፡ የኤርምያስ ኹለተኛው ደቀ መዛሙር በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ባሮክ ስም መጠራታቸው ነው፤

፪ተኛው. ባሮክ ኦባማ፡ አዲስ አበባ የገቡበት ቀን፡ ሓምሌ ፲፱ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት ሲኾን፡ ይህ ዕለት፡ ራሷ፡ "ኢትዮጵያ" የኾነችው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም አብሣሪዋና ባለሟሏ የኾነው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ከእርሱ ጋር፡ ዓመታዊ በዓላቸው የሚከበርላቸውን፡ ኢትዮጵያዊዉን ሕፃን ሰማዕት፡ ቅዱስ ቂርቆስንና እናቱን ሰማዒት፡ ቅድስት ኢየሉጣን የመሰሉትን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ ታማኞች አገልጋዮችን፡ ከመከራ እሳት ያዳነበት ነው።

ከአገራቸው ታሪካዊ ልምድ በመነሣት፡ ባሮክ ኦባማ፡ በይፋ በሚታወቁበት ማንነታቸውና ምንነታቸው ምክንያት፡ በተለይ፡ "ለዚህ፡ አኹን ለሚገኙበት ታላቅ ሥልጣን፡ በምንም መሥፈሪያ ይበቃሉ!" በማይሏቸው ዘንድ፡ ደኅንነታቸውና ሕይወታቸው፥ እስካኹን፡ ሙከራው እንኳ ሳይታይ፡ እንዳለ ተጠብቀው፡ ከአጥፍቶ ጠፊ አደጋም ሳይቀር፡ ተከልለው ሊድኑ የቻሉት፡ በእግዚአብሔር መላእክት ካልኾነ በቀር፡ በሌላ፡ በማንም ሰብአዊ ኃይል፡ አለመኾኑን ለማመን፡ ለማንኛውም የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ከቶ አያዳግትም።

ስለዚህ፡ ክቡር አቶ ቡሩክ ኦባማ፡ አዲስ አበባ የገቡበት፡ ራሱ ዕለቱ፡ የተቀዳጀው፡ ይህ ልዩ ምልክትነት፡ እርሳቸው፡ እስካኹንና ወደፊትም፡ በደኅንነታቸውና በሕይወታቸው፥ እንዲህ ተጠብቀው ያሉት፡ ለታማኞች አገልጋዮቿ፡ ከሰውነታቸው ሳትርቅ፡ የዘወትር ጥላ ከለላ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኑን፡ ያለጥርጥር ለማሳወቅ ነው።

፫ተኛው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ይህንኑ ልጇንና ዜጋዋን፡ በክብር በምትቀበልበት ጊዜ፡ በአዲስ አበባ ከተማዋ ሰማይ ላይ የታየው፡ ተአምራዊና መልእክታዊ ትንግርት ነው፤ ያም ትንግርት፡ ይኸው፡ የኢትዮጵያን መሬት በረገጡበት ሰዓት፡ ርእሰ-ብሔራዊው ጥያራቸው ጭምር ለማረፍ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ፡ በከባድ ዝናብ መካከል፡ በሰማይ ላይ የተቀሠተው፡ የዚችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኪዳናዊ ሰንደቅ ዓላማ የኾነው፡ የኖኅ ቀስተ ደመና፡ በምሥራቅ አግጣጫ ባለው፡ የኅዋ ሰሌዳ ላይ፡ ከምድር እስከምድር ዳርቻ ተተክሎ መታየቱ ነው፤ (ተረፈ ኤር. ምዕ. ፰-፲። ዘፍጥ. ፱፥ ፰-፲፯።)

ይህንም፡ እውነታ፡ ከዚህ ጋር አያይዘን ያበረከትናችሁ፡ ብርሃናውያን ሥዕሎች፡ በከፊል ያረጋግጣሉና፡ ተመልከቷቸው!

፬ተኛው፡ ይህን ኹሉ፡ መለኮታዊ ትንግርት፡ በእርሱ አገልጋይነትና መሣሪያነት፥ በእርሱም፡ የሥልጣን ጊዜ ይፈጸም ዘንድ፡ የውስጥ እውነተኛ ማንነቱንና ምንነቱን፡ እርሷ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ብቻ የምታውቀውን፥ በስም አጠራሩም፡ የእርሷን መለኮታዊ ባለቤትነትና የበላይ መሪነት መልእክት ልታስተላልፍ የመረጠችው፡ አንዱ ልጇ፡ "ኃይለ ማርያም"፡ በኢትዮጵያዊ ስሙ፡ "ቡሩክ/ባሮክ" የተባለ፡ እንግዳ ልጇን፡ በዚህ ረገድ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ባሳየችውና ባደረገችው ትንግርት፡ "ደስ አለኝ!" ብሎ፡ ማስተናገዱን ለማመልከት ነው።

ይህም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነቱንና ምንነቱን፡ በሥውር ብቻ ሳይኾን፡ በይፋም ጭምር በመካድ፥ የአምልኮ አመንዝራነትንም፡ በዚሁ መልክና ይዘት በመፈጸም፡ በእርሷ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ፡ ታላቁን፡ የዓመፅና የክፋት ኃጢአት ያደረገውን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን፡ ይህንኑ፡ የዛሬውን ትውልድ፡ እንደፍላጎቱና እንደምርጫው፡ ለመቅጣት፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ትውልዱ ራሱ፡ ኰትኵቶትና አሳድጎት ለነበረው፥ በመጠሪያ ስሙም፡ "መንግሥቱ፡ የኃይለ ማርያም ነው!" ላስሰኘው፡ ለሌላው፡ ለቀደመው ልጁ፡ በ፲፱፻፳፮ ዓመተ ምሕረት፡ አሳልፋ ሰጥታው እንደነበረው፡ ማለት ነው።

፭ተኛው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእኒህ ኹሉ ተጠሪዎች ልጆቿ በፊት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓቷ በጸናባትና ስሟ በተጠራባት አገር ላይ ሠይማቸው፡ (ሾማቸው) የነበሩት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ መላዎቹን አፍሪቃውያን ልጆቿን፡ በተጠሪዎቿ አማካይነት አሰባስበው፡ ያደራጁቸው ዘንድ፡ በሰጠቻቸው መመሪያ መሠረት፡ ይህን፡ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፡ በመናገሻ ከተማዋ፡ በአዲስ አበባ ለማቋቋም መብቃታቸው፥ እንዲህ ኾኖ የተቋቋመውም ድርጅት፡ ዓላማዎቹን፡ በተግባር ላይ እያዋለ መቀጠሉ፡ ይኸው፡ በገሃድ የሚታይ ነው።

ይህም ኹሉ የኾነው፡ የእርሷን፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ እውነተኛ ማንነትና ምንነት፡ ለእነዚሁ አፍሪቃውያን ልጆቿና ለቅኝ ገዢዎቻቸው፥ ለመላውም ዓለም ጭምር፡ በይፋ በማሳወቅና አርአያነቷን በመግለጽ፡ በክፉዎች ባዕዳን፡ ልዩ ልዩ የግፍ አገዛዝና የባርነት ቀንበር ሥር፡ ተጨቍነው፡ ሲማቅቁ የኖሩትን፥ እነዚህኑ፡ በመላው የአፍሪቃ ክፍለ ዓለሟ ተበትነው የሚሠቃዩትን ልጆቿን፡ በቅድሚያ፡ ነጻ ከማውጣት ጋር እንደነበረ፡ ይታመናል።

፮ተኛው. ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለመላዎቹ የአፍሪቃ ክፍለ ዓለም ልጆቿ፡ ለሴቶቹም፥ ለወንዶቹም፡ ልታስተላልፈው የሚያስፈልጋትን፥ ይህንኑም፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ጀምሮ እስከዛሬ ያሉት፡ ሥጋውያኑም ኾኑ፡ መንፈሳውያኑ ተጠሪዎቿ፡ ከእርሷ፡ የተሰጣቸውን ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት፥ የተጣለባቸውንም አደራቸውን ባለመጠበቅ፡ ኾን ብለው፡ ሳያስተላልፉላት ያቆዩዋቸውን መልእክቶቿን፡ እነሆ፡ አኹን፡ ጊዜው ስለደረሰ፡ ለዚህ አገልግሎት የጠራቻቸው፡ ኢትዮጵያዊ ልጁ ባሮክ ኦባማ፡ ዛሬ፡ እንዲህ፡ በዚሁ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፡ የጉባኤ አዳራሽ ተገኝተው፡ ኢትዮጵያዊ ተልእኳቸውን ሊፈጽሙ መብቃታቸው፥ ተልእኳቸውንም፡ በዚህ መልክና ይዘት ሊያከናውኑ መቻላቸው ነው።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእኒህ ኢትዮጵያዊ ልጇ፡ በባሮክ ኦባማ መልእክተኛነት፡ ይህን ተልእኮ ባስፈጸመችበት ጊዜ፡ ራሳቸው፡ ቡሩክ ኦባማ፡ ሊናገሩትና ሊያስተላልፉት ያሰቡትንና ያቀዱትን፥ ተዘጋጅተውም የመጡበትን፥ በእርሷ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ግን፡ በተለይ፡ አግባብነት የሌላቸውንና ጸያፍ የኾነውን ኹሉ አስትታ፡ የእርሷ የኾኑትን፡ መልእክቶች ብቻ እንዲናገሩና እንዲያስተላልፉ ማድረጓ፡ እዚህ ላይ በአጽንዖት ሊወሳ ይገባል።

ይህ ኹሉ መለኮታዊ ትንግርት የታየበት፥ ክቡር አቶ ባሮክ ሁሴን ኦባማም፡ ኢትዮጵያዊ ተልእኳቸውን በመፈጸም፡ እንዲህ፡ በዚሁ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፡ የጉባኤ አዳራሽ ተገኝተው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለመላው የአፍሪቃ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቿ ያዘጋጀችውን፡ ይህን መልእክቷን ለማስተላለፍና ለማድረስ የበቁበት፥ በመጨረሻም፡ የመጡበትን አገልግሎትም፡ በዚህ መልክና ይዘት ካከናወኑ በኋላ፡ የእንግድነታቸው ማብቂያ ኾኖ፡ በሰላም የተሸኙበት ዕለት፡ ራሷ፡ "ኢትዮጵያ" የኾነችው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዓልዋ የሚከበርበት፡ በሓምሌ ፳፩ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት መኾኑ፡ ለትንግርቱ ተጨማሪ ሞገስና ጽንዐ ኾኖታል።

፯ተኛው፡ ለዚህ ኹሉ ትንግርታዊ ኹኔታ፡ መቅድም የኾነውን፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፡ ከዚህ አከታትለን፡ ባጭር እናሳውቃችኋለን፤ ይኸውም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ መደበኛ አገልጋይ የኾነው፡ የዚህ መልእክት ጸሓፊ፡ በዚሁ ተልእኮው ረገድ፡ በ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ ቆይታ አድርጎ ሣለ፡ የኾነውንና የደረሰውን ነክ ኹኔታ፡ የሚያወሳው ዝክረ-ነገር ነው።

አዎን! ያ ጊዜ፡ የዚሁ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ አገር፣ ሕዝብና መንግሥት፡ ጽዋው እየሞላ በኼደው ብዙ ኃጢአታቸው ምክንያት፡ ወደፊት ሊደርሱባቸው የሚችሉ የቅጣት መቅሠፍቶች እየጠበቋቸው መኾኑን በማስጠንቀቅ፡ ከእነዚሁ መዓቶች ለመዳን፡ ንስሓ ይገቡ ዘንድ፡ ይኸው አገልጋይ፡ አያሌ ምክሮችንና ማስጠቀቂያዎችን የያዘውን Ethiopia: The Classic Case የሚለውን መጽሓፉን አሳትሞ ያሠራጨበት ወቅት ነበር።

እንዲህ፡ የኋላኋላ፡ በዚህ ስያሜ፡ በመጽሓፍ መልክ ከመታተሙ በፊት፡ የዚሁ መልእክት፡ ሙሉው መድበል ጽሑፍ፥ THE DIVINE TRUTH ABOUT ETHIOPIA AND ETHIOPIANISM በሚል ርእስ፡ የተዘጋጀ ስለነበረ፡ የዚህኑ ጽሑፍ አንድ ቅጂ፡ ይኸው አገልጋይ፡ በጊዜው፡ ያገሩ ርእሰ ብሔር ለነበሩት፡ ለክቡር ምስተር ዊልያም ጄ. ክሊንተን፡ በእነርሱ አቈጣጠር፡ በAugust 21, 1996 ከተጻፈ ደብዳቤ ጋር፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ ስም ላክ።

ይኸው ጽሑፍ መልእክት የተላከው፡ በእነርሱው የደብዳቤ ቤት በኩል በመኾኑ፡ መድረሱና መቀበላቸው፡ የታመነ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ በእነርሱ በኩል፡ በብጣሽ ክርታስ ጽፈው በመላክ እንኳ፡ ይህንኑ የሚያረጋግጥ አንዳችም መልስን ሳይሰጡት በመቅረታቸው፡ የሌሎች አገሮች መሪዎች ያከበሩትን ሥነ ሥርዓት፡ እነርሱ ግን፡ አቃልለውና ንቀው እንደተዉት ተረዳ። -ንቀት አንድ!

ያን፡ የኢትዮጵያ፡የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክቱን፡ ለዚያ አገር፥ ሕዝብና መንግሥት፡ በበኩሉ እንዳደረሰ፥ ተልእኮውንም እንደፈጸመ በመቍጠር፡ ይኸው አገልጋይ፡ ወደብሔረ ሙላዱ፡ ወደ"ኢትዮጵያ" ምድር ተመለሰ። (Ethiopia: The Classic Case pp. 209, 215.)

ተመልሶም ሣለ፡ ወዲያው፡ የመስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረትን፡ ኢትዮጵያዊ የዐውደ ዓመትና የእንቍጣጣሽ በዓሉን፡ በቤቱ በሚያከብርበት ሰዓት፡ እርሱ፡ ከአምስት ዓመታት በፊት፡ በዚያ የጽሑፍ መልእክቱ ያስጠነቀቀው፡ ያ አስደንጋጭና አሠቃቂ ታላቅ ዕልቂት፡ በእነርሱ አቈጣጠር፡ በSeptember 11, 2001፡ በኒው ዮርክና በዋሽንግተን ከተማዎቻቸው ላይ ሲደርስ፡ ይኸው አገልጋይ፡ በነፋስ ድምፅ ሰሌዳ ላይ፡ ድንገት ተመለከተ።

በዚያን ጊዜም፡ በአንድ በኩል፡ ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን የምሕረት ምክርንና የንስሓ ማስጠንቀቂያን ባለመስማታቸው፡ ከኖኅ እስከሰዶምና ገሞራ፥ ከዚያም፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በየዘመናቱ፡ እየደረሰባቸው በሚታየው፡ ጥፋትና ድምሳሴ፡ ከማዘንና ከመተከዝ በቀር፡ ሌላ፡ ምንም ሊያደርግ የማይችል፡ ዐቅመ-ቢስ መኾኑን፡ ይኸው አገልጋይ፡ ለራሱ ተገነዘበ።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በአገልጋዮቹ አማካይነት የሚያስተላልፈው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ሰዎች፡ ቢያቃልሉትና ቢንቁትም እንኳ፡ ምንጊዜም፥ በምንም መንገድ ሊታበልና ሊሻር የማይቻል፡ ፍጹም እውነት መኾኑን ስላረጋገጠለት፡ ይኸው አገልጋይ፡ በኾነው ኹሉ እየተገረመና እየተደነቀ፡ ለዚህ ቸር ፈጣሪው፡ ልባዊ ምስጋናውን አቀረበ።

ከዚህም ጋር፡ ጣዖታዊው የዲያብሎስ አምልኮ ወደሚፈጸምባት፡ ወደታኅሣሥ ወር፡ በክፉ ሰዎች እንድትዛወር የተደረገችው፡ ያች፡ ቀድሞ፡ የፍጥረተ ዓለሙ፥ የአዳምና ሔዋንም፥ ኋላም፡ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና የተወዳጅ ልጇ፡ የኢየሱስ መሢሕ የልደት ዕለት የኾነችው፡ መስከረም ፩ ቀን፡ ለዚህ፡ የቅጣትና የምሕረት መለኮታዊ ትንግርት፡ ለምን ተመረጠች? ብሎም፡ ይኸው አገልጋይ፡ በአንክሮና በተዘክሮ ኀሊና ተመሰጠ።

ይህንኑ በተመለከተ፡ በቅድሚያ፡ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን፥ ሕዝባቸውንና መንግሥታቸውንም፡ "እግዚአብሔር ያጽናናችሁ! ያበርታችሁም!" ብሎ፡ በመንፈስ፡ የመከራቸው ተካፋይ መኾኑን ለመግለጽ፥ ቀጥሎም፡ ያለፈውንና ይህ የደረሰውን ታላቅ ጥፋት በማዘከር፥ መቀጣጫ አድርጎ፡ ንስሓ በመግባትም፡ ለወደፊቱ፡ ሊያደርጉት የሚገባውን ክርስቲያናዊ ጥንቃቄና ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በይበልጥ ገልጦ ለማሳሰብ፡ ይኸው አገልጋይ፡ ተገቢውንና አስፈላጊውን መልእክት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስም፡ በመስከረም ፲ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓ. ም. ይኸውም፡ በSeptember 20, 2001፡ በተጻፈ ደብዳቤ፡ በዘመኑ፡ ያገሩ ርእሰ ብሔር ለነበሩት፡ ለክቡር ምስተር ጆርጅ ደብልዩ ቡሽ አስተላለፈ። የዚህ ደብዳቤ ቅጂ፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይገኛልና፡ መመልከት ነው።

እኚሁ፡ ክቡር ምስተር ጆርጅ ደብልዩ ቡሽ፡ ይኸው አገልጋይ ለጻፈላቸው፡ ከላይ ለተጠቀሰው ደብዳቤ፡ ያለፉት የሥልጣን እኩያቸው፡ ክቡር ምስተር ዊልያም ጄ. ክሊንተን እንዳደረጉት ኹሉ፡ አኹንም፡ ለዚሁ አገልጋይ፡ አንዳችም ዓይነት መልስ ሳይሰጡት ቀሩ። -ንቀት ኹለት!

እነዚህ ኹለት የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ርኡሳነ ብሔሮች፡ ይኸው አገልጋይ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስም፡ ለእያንዳንዳቸው ለላከላቸው ደብዳቤ፡ "ደርሶኛል!" በሚል መልክ እንኳ፡ ምንም ዓይነት መልስ አለመስጠታቸው፡ የምግባራቸውን ሥነ ሥርዓታዊ ጒድለት የሚያሳይ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ ትችት ሊሰጥበት፥ በተራ ቊም ነገርነትም እንኳ ሊፈረጅ የሚገባው አይደለም።

በእነርሱ ዘንድ፡ የእነርሱን ያፌታዊነት፡ ከፍ አድርገው፥ ካማዊነትን፥ ሴማዊነትንና ያፌታዊነትን አዋሕዶ የያዘውን፡ የእርሱን ኢትዮጵያዊነት ደግሞ፡ በንቀት ዝቅ አድርገው፡ ማዋረዳቸው ነው። ምናልባት ወገኖቻቸው፡ በካማውያን ላይ ሲያካኺዱት የኖሩት፡ ይኼ ዓይነቱ ያላዋቂነት ክፉ ልማዳቸው አልለቅ ብሏቸው፡ በአኹኑ ጊዜ ደግሞ፡ ይህንኑ ያረጀና ያፈጀ፥ የሞተም ድርጊት፡ በኢትዮጵያዊው አገልጋይ ላይ ሊፈጽሙ ከጅለው ከኾነ፡ ይኼ፡ እንግዴህ ወዲህ የማያስኬድ፥ የማይቻላቸውም መኾኑን፡ ሊገነዘቡት ይገባቸዋል።

ይህን የመሰለው ክፉ አስተሳሰብና አደራረግ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ቦታ የለውም፤ አይፈቀድምም። ፀረ-እግዚአብሔራዊ እና ኢተፈጥሮአዊ የኾነው፡ ይኼ ክፉ ልማዳቸው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ተሽሮ ተወግዷል። ይህም እውነታ፡ እነሆ፡ በኢትዮጵያዊው ባሮክ ሁሴን ኦባማ ታላቅ ሹመትና በአኹኑ፡ በተሳካው፡ የኢትዮጵያ ጒብኝታቸው፡ ተረጋግጦ አልቆለታል።

ይኸው አገልጋይ፡ ለመላው ዓለምና ለዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሕዝቦች እንዲያደርስ፡ ከ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የተሠየበትን ተልእኮ ለማጠቃለል፡ ለመጨረሻ ጊዜ፡ ወደዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ተመልሶ ኼዶ፡ ተስፋ ባለመቁረጥ፡ አኹንም፡ በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ስም፡ በታኅሣሥ ፯ ቀን፥ ፳፻፫ ዓ. ም. ይኸውም፡ በDecember 16, 2010፡ ለዛሬው፡ የአገሪቱ ርእሰ ብሔርና መሪ፡ ለክቡር ምስተር ባሮክ ሁሴን ኦባማ፡ የጻፈላቸው ግልጽ ደብዳቤ፡ ከነዐባሪዎቹ፡ ከዚህ መልእክት ጋር ተያይዞ ቀርቧል። እርሳቸውም፡ ከነባለቤታቸው፡ የሰጡት መልስ፡ ዐብሮ ይገኛልና፡ ኹሉንም፡ ተመልከቷቸው!

**- ሰይጣናዊው ንቀት ተወግዶ፡ በአምላካዊው አክብሮት ተተካ!**

በዚያ፡ ለእርሳቸው በተጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ከተጠቀሱት የቍም ነገር አሳቦች በቀር፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ከዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ጋር የተቀናጀውን፡ የመላው ዓለምን አሥጊ ኹኔታ በሚመለከት፡ ተጋርጦ ላለው ውስብስብ ችግር፡ በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** በኩል ሊቀርቡላቸው የሚገቡ፡ ሌሎች መፍትሔዎችም መኖራቸው፡ በአጽንዖት ተገልጾላቸው ነበር፤ ስለዚህ፡ አስፈላጊ መስሎ ከታያቸው፡ ለዚሁ ተልእኮ፡ ለጊዜው፡ በቅርባቸው የሚገኘውን፡ የዚችው፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ** መልእክተኛ የኾነውን፡ ይህንኑ ኢትዮጵያዊ አገልጋይዋን ተቀብለው እንዲያነጋግሩ፡ መልካም ፈቃዳቸው ተጠይቆ ነበር።

ነገር ግን፡ በዚያን ጊዜ፡ በእርሳቸው በኩል፡ በዚህ፡ እግዚአብሔራዊ ዕድል፡ ሊጠቀሙ አለመፈለጋቸውን፡ በዚያች አጭር፡ የክርታስ መልሳቸው፡ በሚበቃ አሳወቁ።

ይኸው ኢትዮጵያዊው አገልጋይ መልእክተኛ፡ አኹንም፡ ተስፋ ባለመቍረጥ፡ በተልእኮው ጸንቶ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ በተለይ፡ እስልምናን በሚመለከት፡ ለእኒሁ፡ ለክቡር፡ ርእሰ ብሔር ባሮክ ኦባማ የምታቀርብላቸው፡ የተጨበጡ፡ የመፍትሔ ሓሳቦች ስላሉ፡ "ምናልባት፡ እነርሱን ወደመቀበሉ ያዘነብሉ ይኾናል!" በሚል ግምት፡ በዚያ፡ የሚያደርገውን ቆይታ አራዘመ።

ጽኑ ተስፋውም፡ እኚሁ፡ ክቡር፡ ርእሰ ብሔር ባሮክ ኦባማ፡ እየተፋፋመ በመኼድ ላይ ያለውን እውነታ ተገንዝበው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ የምታቀርብላቸውን አማራጭ አሳቦች፡ ሌላው ቢቀር፡ ለማዳመጥ፡ "ፈቃደኛ ይኾኑ ይኾናል!" በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነበር። ነገር ግን፡ ባለመታደል፡ ያ፡ ሊኾን አልቻለም።

በዚህ አንጻር፡ በእርሳቸው ዘንድ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን ያገኘው የመፍትሔ ሓሳብ፡ እስካኹን፡ በአንድ በኩል፡ በዓለማውያኑና በሥጋውያኑ ሰዎች፡ የፈሊጥ ብልህነትና የዕውቀት ልሂቅነት፥ በአገራቸውም፡ የገንዘብ ብልጽግናና የጦር ኃያልነት በመተማመን፥ በሌላ በኩል ደግሞ፡ በሃይማኖታውያኑና በመንፈሳውያኑ ክርስቲያኖች የድጋፍና የተባባሪነት ምዕዳን (ምክር-ዐዘል ማስጠንቀቂያ) በመታገዝ፡ የሚያካኺዱቸውን፡ የተግባር ግዳጆች፡ በበለጠ ጽናት እንዲቀጥሉ ማድረግን መኾኑ፡ በእርግጠኛነት ታወቀ።

ይህ ምርጫ ደግሞ፡ ይኸው እንደሚታየው፡ ያለውን አሥጊ ኹኔታ፡ እየተባባሰ እንዲኼድ ከሚያደርግ በቀር፡ በሰው ሕይወትና በቋሚ ንብረት ጥፋት ረገድ፡ ለአያሌ ዐሥርተ ዓመታት፡ ያለማቋረጥ እየተከፈለ ያለውን መሥዋዕትነትና ጥረት ኹሉ፡ ቅንጣት ያህል እንኳ፡ ወደፍሬያማ ሥምረትነት ሊያቃርበው እንዳልቻለ፡ ይኸው፡ በገሃድ የሚታይ ኾነ።

የክቡር፡ ርእሰ ብሔር ባሮክ ኦባማ፡ መልሳቸው፡ ምንም ይኹን ምን፡ ያንኑ ለማግኘት፡ ይኸው አገልጋይ፡ ለሚበቃ ጊዜ፡ ጠበቀ። ነገር ግን፡ በእርሳቸው በኩል፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ልታቀርብላቸው ያዘጋጀችውን አማራጭ አሳብ፡ ሌላው ቢቀር፡ ለማዳመጥ እንኳ፡ ፈቃደኛ አለመኾን ብቻ ሳይኾን፡ ፍላጎቱም እንደሌላቸው ሲያረጋግጥ፡ ይኸው አገልጋይ፡ በቅርቡ፡ ብሔረ ሙላዱ ወደኾነችው፡ ወደኢትዮጵያ ምድሩ ተመለሰ።

ይኸው አገልጋይ፡ ወዲያው፡ ወደብሔረ ሙላዱ እንደተመለሰ ደግሞ፡ በመስከረም ፩ዱ፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት፥ እንደነሱ ዘይቤም፡ በNine-Eleven፡ 2001 እንደኾነውና እንደተሰማው፡ እንደቀደመው አስደንጋጭ መርዶ ሳይኾን፡ ሌላ ምሥራችን ሰማ።

ያም ምሥራች፡ በዚያ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ መልእክተኛ እና በእኚሁ፡ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ኦባማ፡ በመጨረሻ፡ ተፈጽመው በታዩት፡ ተነጻጻሪ ድርጊቶች፡ የታየው ትንግርት ነው።

ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሕዝብና መንግሥት መልካምነትና ደኅንነት ስትል፡ ወደእነርሱ ልካው የነበረው፥ ነገር ግን፡ ይህንኑ መልእክቷን፡ በዚያ አገራቸው አድርሶ፡ ተልእኮውን በሚፈጽምበት ጊዜ፡ የቀደሙት ኹለት አቻዎቻቸው እንዳደረጉት ኹሉ፡ አኹንም፡ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ሁሴን ኦባማ፡ እርሱን ተቀብለው ለማነጋገር ያልፈለጉት፡ ያ፡ አገልጋይ መልእክተኛዋ ያለበት ሲኾን፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ያን የመሰለ አቋም ይዘው የነበሩት፡ እኚሁ፡ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ኦባማ የሚገኙበት ነው።

ትንግርቱም፡ በቃል መነጋገርን የተነፈገው፡ ይኸው፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይና መልእክተኛ፡ "ና! በቃህ!" ተብሎ፡ ወደብሔረ-ሙላዱ ከተመለሰ በኋላ፡ በአዲስ አበባ ሣለ፥ "የለም! አላነጋግርህም!" ያሉት፡ እኝሁ፡ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ሁሴን ኦባማ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ያላቸውን ታዛዥ ልጅነት በማረጋገጥ፥ እርሳቸውም፡ ከእርሱ፡ ብዙም ሳይቆዩ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የይፋ ግብዣና ጥሪ፡ ወደምድረ ርስታቸው ኢትዮጵያ፡ እርሱን ተከትለው መምጣታቸውና የመጡበትን፡ የእርሷን ተልእኮ ፈጽመው፡ ወደበአታቸው መመለሳቸው ነው።

## መደምደሚያ

ሐተታችንን ለመደምደም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተቃዋሚዎች ዘንድ፡ በምናውቃቸው አያሌ ምክንያቶቻቸው የተነሣ፡ "ምንጊዜም አይደረግም! ሊደረግም አይገባም! ምናልባትም፡ ሊደረግ፡ አስፈላጊ ቢኾን እንኳ፡ ሊደረግ ይገባ የነበረው፡ ቀደም ብሎ፡ በተለይ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዘመን ነበር!" የሚባልለት፡ ይህ፡ በክቡር አቶ ባሮክ ሑሴን ኦባማ፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ርእሰ ብሔር የተፈጸመው፡ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ይፋዊ ጒብኝት፡ በመሠረቱ፡ ለምን ኾነ? እንዴትስ፡ ሊኾን ቻለ? ለምንስ፡ እስከዛሬ ድረስ ሳይኾን ቆይቶ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሳይታሰብ፡ በድንገት ኾነ?

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱ፡ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም፡ ከላይ በተሰጠው ሐተታ እንደተብራራው፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ ትክክለኛውን ዕለት መግለጽ ካስፈለገም፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት፡ ለመላው ፍጥረተ ዓለሚ ባስተላለፈችው፡ የዐዋጅ ቃሏ፡ ራሷን የከሠተችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለተቃዋሚዎቿ ብቻ ሳይኾን፡ ተሠውራበት ለኖረችበት፡ ሰብአዊ ወገን ኹሉ፡ ማንነቷንና ምንነቷን የገለጠችበት እውነታ መኾኑ ነው።

ይህም እውነታ፡ መላው ፍጥረቷ፥ በተለይም፡ ሰብአዊው፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ቢሰማም፡ ባይሰማም፥ እንዲህ፡ በገሃድ ኾኖና በተጨባጭ ተደርጎ ያየውን፡ አስተውሎ መቀበል ከቻለም፡ ካልቻለም፥ ቢያምንም፡ ባያምንም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሥጋዊዉንም ኾነ፡ መንፈሳዊዉን ፍጥረት፡ በሙሉ በሚመለከት፡ በኹሉ ላይ፡ በአጠቃላይ ያላትን፡ ፈጣሪነቷንና ባለቤትነቷን፥ የበላይነቷንና ተቆጣጣሪነቷን፥ መሪነቷንና አስተዳዳሪነቷን፥ ጠባቂነቷንና መጋቢነቷን፥ ቸርነቷንና በረከቷን፥ ጸጋዋንና ምሕረቷን፥ እውነቷንና ዕውቀቷን፥ ሰላሟንና ፍቅሩዋን፡ ሥልጣኗንና ኃይሏንም፡ ለራሱ ለመላው ፍጥረተ ዓለም፡ እንደገና አረጋግጣ ለማሳየትና ለማስረዳት፥ ለማስገንዘብና ለማሳመንም፡ ይህ፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ሁሴን ኦባማ፡ የኢትዮጵያ ጒብኝት፡ በቂ መጽሔትና ምስክር ኾኗታል።

## እናስተውል

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይዋና መልእክተኛዋ የኾነው፡ ይህ ኢትዮጵያዊ እና እኝህ፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ርእሰ-ብሔር ባሮክ ሁሴን ኦባማ፥ ሌላውም ሰብኣዊ ፍጡር፡ ወንዱም፥ ሴቱም፥ ሴማዊዉም፥ ካማዊዉም፣ ያፌታዊዉም፥ አረማዊዉም፥ ይሁዲዉም፥ ክርስቲያኑም፥ ሙስሊሙም፥

ኹሉም፡ በእየራሳቸው የክህደት አስተሳሰብ፡ እየራሳቸውን ለውጠው፡ አኹን ላሉበት የሓሰት ማንነትና ምንነት እየራሳቸውን ካልዳረጉ በስተቀር፡

እያንዳንዳቸው፡ ከፈጣሪያቸው የተቀዳጁት፡ እውነተኛ ማንነታቸውና ምንነታቸው፡ ምን ዓይነት እንደኾነ የሚያሳውቀው፡ የቅዱሱ ኪዳን ጸሎታችን ቃል፡ ይኸውላችሁ!

**በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፤ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ/ሃ ለኢትዮጵያዊ/ት፡ ዘኪዳን ቅዱስ፤ እንዘ በኀቤሁ/ሃ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፣ በአሥረ ተዋሕዶ።**

**ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው/ቷ ሰውነት፤ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።**

**We believe that Ethiopia, as such and in the Ethiopian person of the Holy Covenant, represents the Kingdom of God constituting the three Houses of the People, of the Government and of the Priesthood in the mystery of Unity in Trinity.**

\+ \+ \+